# የዱር እንስሳት ፊልም ቀረፃ

# መመሪያ ቁጥር 845/2014

# የዱር እንስሳት ፊልም ቀረፃ
# መመሪያ ቁጥር 845/2014

በዱር እንስሳትና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የሚደረግ የፊልም ቀረፃ የዱር እንስሳቱን አደጋ ላይ በማይጥልና ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዱር እንስሳት ኢ-ፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልት አማካይነት ከዱር እንስሳት ሃብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማጎልበት ለሀገሪቱ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዱር እንስሳት ፊልም ቀረፃ የሚስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ ወጥነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ቀደም ሲል የወጡትን የዱር እንስሳት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 እና የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ማስፈጸሚያ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 17 (2) በተደነገገው መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የዱር እንስሳት ፊልም ቀረፃ መመሪያ ቁጥር 845/2014” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"አዋጅ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/199 ነው፤

2. **"ደንብ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 163/2001 ነው፤
3. በአዋጁ እና ደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
4. **"ፊልም ቀረፃ** "ማለት ማንኛውም በዱር እንስሳቱና የተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸው ላይ ለንግድ ዓላማ የሚከናወን የፊልም ሥራ ነው
5. "**ፈቃድ**" ማለት ለፊል ቀረፃ ሥራ ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
6. **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤
7. **"ባለስልጣን"** ማለት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡
8. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

1. የዱር እንስሳት ሀብታችንን በአግባቡ ለማስተዋወቅ የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ ፊልም እንዲኖር፣ የዱር እንስሳት ፊልም እንዲስፋፋና የበኩሉን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲያበረክት ሁኔታዎችን እንዲመቻች ማድረግ፤
2. የዱር እንስሳት ፊልም ጥራትን በሚመለከት ተገቢውን ክትትል ለማድረግና የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤
3. የዱር እንስሳት አቀፍ ፊልም ሥራን ለማሳለጥ፣ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት፣ ክፍተቶችን ለመዝጋትና ወጥነት ያለውን አሰራር መዘርጋት፤
4. በፊልም ቀረፃ ምክንያት የዱር እንስሳት ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ መቀነስ፤

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በፌደራል መንግስት በሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ ፊልም ለንግድ ሥራ ዓላማ በሚቀረጽ ሰው ላይ እና በየትኛውም የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ላይ ፊልም በሚቀርፅ የውጭ ሃገር ዜጋ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የዱር እንስሳት ፊልም ቀረፃ ሥራ

### 5. መሠረት

1. ማንኛውም ሰው በዱር እንስሳት የፊልም ቀረፃ ሥራ ላይ ለመሰማራት ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ በአየርና በየብስ እንዲሁም በውሃ አካላት በመንቀሳቀስና የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎችን በመጠቀም በዱር እንስሳትና በመኖሪያቸው አካባቢያቸው ለሚቀረጹ የፊልም ሥራዎች ፈቃድ ይሰጣል፡፡
3. ባላሥልጣኑ በሚያቋቁመው የቴክኒክ ቡድን የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተመስርቶ ለማስታወቂያ ሥራ፣ ለትምህርታዊ፣ ለሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር አገልግሎት ለሚውል የፊልም ቀረጻ ልዩ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
4. አንድ የጥበቃ ቦታ ፊልም ለመቅረጽ የሚከፈል የአንድ ጊዜ የፈቃድ ክፍያ የሚያገለግለው አንድ የጥበቃ ቦታ ፊልም ለመቅረጽ ብቻ ሆኖ ለምድር ፊልም ቀረጻ እስከ 30 ቀን እና ለአየር ላይ ፊልም ቀረጻ እስከ 20 ቀን የቆይታ ጊዜ ይኖረዋል፡፡

### 6. የፊልም ቀረፃ ፈቃድ መስፈርቶች

ፊልም ለመቅረፅ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

1. የሥራውን ጭብጥ የሚመለከት ዝርዝር ኘሮግራም እና ፕሮጀክት ፕሮፖዛል፣
2. የፊልም ባለሙያ ስለመሆኑ ወይም የፊልም ባለሙያ ስለመቅጠሩ የሚገልጽ የስምምነት ውል፤
3. ከመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ፊልም የማንሳት ፈቃድ፤
4. በአውሮኘላን የዱር እንስሳትን በፊልም ለመቅረፅ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠ ፈቃድ፣ ከባለሥልጣኑና ከአየር ኃይል አግባብነት ያላቸው ባለሙያዎች ማሳተፍ፤

7. <u>ስለጥያቄ አቀራረብ</u>

1. ለፊልም ቀረፃ ሥራ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማመልከቻና አስፈላጊ መረጃዎችን በማሟላት ሥራውን ከመጀመሩ ከሁለት ሳምንታት በፊት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ የቀረበውን ማመልከቻ ገምግሞ በአንድ ወር ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡
3. አመልካቹ የፊልም ቀረፃ ፈቃድ ክፍያ በደንቡ መሠረት ይፈጽማል፡፡
4. የቀረበው ጥያቄ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ በ15 ቀን ውስጥ መረጃውን አሟልቶ እንዲያቀርብ ይመለስለታል፡፡
5. ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መረጃውን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡

8. <u>ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታ</u>

1. ፈቃዱን ለተሰጠው ዓላማና ተግባር የማዋል፣
2. የፊልም ቀረፃው የዱር እንስሳቱንና የመኖሪያ አካባቢያቸውን የማይረብሽና የማይበክል እንዲሁም በዱር እንስሳቱ ባህሪ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በማይፈጥር ሁኔታ የማከናወን፤፡
3. ከፊልም ቀረፃ በፊት የሚጠበቁበትን ክፍያዎች በቅድሚያ የመክፈልና አስፈላጊ የጥበቃ ቦታዎች መግቢያ ፈቃድ የማሟላት፤
4. የፊልም ሥራውን የብቃት ማረጋገጫና የሥራ ፈቃድ በሚያቀርብ ባለሙያ ብቻ የማከናወን፤
5. ባለሥልጣኑ ይህን መመሪያ መሠረት አድርጎ የሚያዘጋጀውን ውል የመፈረምና የመተግበር፣
6. የሙያውን ሥነ-ምግባር የማክበር፣
7. በተፈቀደለት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ብቻ የፊልም ቀረፃውን የማካሄድ፤
8. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው ወይም በሀገር ውስጥ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሕጋዊ ጉዳይ አስፈጻሚና ሕጋዊ አስጐብኚ ድርጅት የመጠቀም፤
9. ከ5 /አምስት/ ያልበለጡ የፊልም ቀረጻ ቡድን አባላትን የመጠቀም፤
10. የተሠራው ፊልም አምስት ቅጂ ለባለስልጣኑ የመስጠት፤
11. ስለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጡትን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የማክበር፣

## 9. ስለ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር

1. ባለሥልጣኑ በሥራ ላይ ያሉትን የአገሪቱን የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚመለከቱ ሕጎች፣ ደንቦችንና መመሪያዎች ላይ ፈቃድ ለተሰጠው አካል ግንዛቤ ያስጨብጣል፤
2. ከፊልም ቀረፃው ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር በመሆን አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤
3. ለፊልም ቀረፃ ተግባር ለሚንቀሳቀሱ የፊልም ባለሙያዎች ተቆጣጣሪ የዱር እንስሳት ባለሙያ ይመድባል፤ ለሚመለከታቸው አካላት የድጋፍ ደበዳቤ ይጽፋል፤
4. ባለሥልጣኑ የፊልም ቀረፃ ሥራ በሚከናወኑባቸው ቦታዎች ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 10. ግዴታን ባለማክበር ስለሚወሰድ እርምጃ

ማንኛውም የፊልም ቀረፃ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

1. ከተፈቀደለት ዓላማ፣ ቦታና ጊዜ ውጪ ፊልም ሲቀርፅና የተሰጠውን ፈቃድ ለሕገወጥ ተግባር ሲያውል ከተገኘ የሥራ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡
2. የፊልም ቀረጻው ሲከናወን የዱር እንስሳቱንና የመኖሪያ አካባቢያቸውን የሚረብሽ እና በዱር እንስሳቱ ባህሪ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱ ይሰረዛል፣
3. ከባለሥልጣኑ ጋር የገባውን ውል እንዲሁም ስለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጡትን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተላልፎ ሲገኝ እንደጥፋቱ ክብደት ታይቶ ፈቃዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 11. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የአሰራር ሥርዓቶች ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 12. ቅጣት

ሕጋዊ ፈቃድ ሳይዝ የፊልም ቀረፃ ሲያከናውን የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 13. ቅሬታዎችን ስለማስተናገድ

1. በፈቃድ አሠጣጥም ሆነ መሠረዝ ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በባለሥልጣኑ መልስ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

### 14. ስለተሻሩ ሕጎች

ከዚህ መመሪያ በፊት ወጥተው የነበሩ የዱር እንስሳት ቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ይዞታና አጠቃቀም መመሪያዎች ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

### 15. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

### 16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡